የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6[th] Year No. 15
ADDIS ABABA - 22[nd] December, 1999

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፫/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የጅማ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...................... ገጽ ፩ሺ፪፻፲፪

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 63/1999
Jimma University Establishment Council of Ministers Regulations ...................... Page 1212

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፫/፲፱፻፺፪
### የጅማ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ
### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

#### ክፍል አንድ
#### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የጅማ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፫/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፡

፩· "መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው፤

፪· "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ መሠረት የተቋቋመው የዩኒቨርሲቲው ቦርድ ነው፤

፫· "ጉባዔ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ መሠረት የተቋቋመው የዩኒቨርሲቲው ጉባዔ ነው፤

፬· "የአካዳሚክ ሠራተኛ" ማለት በማስተማር ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሠማራ ሠራተኛ ነው፤

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 63/1999
### JIMMA UNIVERSITY ESTABLISHMENT
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995.

#### *PART ONE*
#### *General*

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Jimma University Establishment Council of Ministers Regulations No. 63/1999."

2. *Definitions*

In these Regulations:

1) "Government" means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
2) "Board" means the University Board established in accordance with Article 6 of these Regulations;
3) "Senate" means the University Senate established in accordance with Article 8 of these Regulations;
4) "Academic Staff" means any employee engaged in teaching or research activities;

፭· "ፕሬዚዳንት" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ መሠረት የሚሾም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ነው፤

፮· "ዩኒቨርሲቲ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ መሠረት የተቋቋመው የጅማ ዩኒቨርሲቲ ነው።

፫· <u>መቋቋም</u>

፩· ጅማ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲው") ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪· ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችን ያካትታል፤

ሀ) ጅማ ጤና ሳይንስ ኢንስቲትዩት፤

ለ) ጅማ እርሻ ኮሌጅ፤

ሐ) ወደፊት በቦርዱ የሚቋቋሙ ሌሎች ፋኩልቲዎችና ኮሌጆች።

፫· የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል።

፬· <u>ዓላማ</u>

ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

፩· ዕውቀትን ማዳበር፣ ማስፋፋትና ማስተላለፍ፤

፪· ከዘር፣ ከብሔር፣ ከፆታ፣ ከሃይማኖትና ከመሳሰሉት አድልዎዎች ነፃ የሆነ በመከባበር፣ መተማመን፣ መተሳሰብና መቻቻል ላይ የተመሠረተና ሁለንተናዊ ስብዕናን የሚያበዕግና የሰው ልጅ ክቡርነትን የሚያጠናክር ትምህርት መስጠት፤

፫· የሥራ ክቡርነትንና የኅብረተሰብ ብልፅግናን የሚያራምድ አስተሳሰብ እንዲሰርጽ ማድረግ፤

፬· የኢትዮጵያን ሕዝብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሥነ ጥበባትና በልዩ ልዩ ሙያዎች የሠለጠኑ፣ ኅብረተሰብን በሚገባ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሰዎች ማፍራት፤

፭· በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች የኅብረተሰቡን ችግር ለመፍታት የሚረዳ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ ጠቃሚ ውጤቶችን ማሠራጨት፤

፮· የክልሉን ሕዝብም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማፋጠን የሚረዱ ሙያዊ ግልጋሎቶች ማበርከት፤

፯· የአገልግሎት ክፍያን በመቀበል የምክርና ሥልጠና አገልግሎት መስጠት።

፭· <u>የዩኒቨርሲቲው ሥልጣንና ተግባር</u>

ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· ፋኩልቲዎች፣ ኮሌጆችና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ተቋሞች ማቋቋምና ማካሄድ፤

፪· የቅድመ ምረቃና የድኅረ ምረቃ ፕሮግራም መቀየስና ሥራ ላይ ማዋል፤

፫· የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤትና አስተዋጽኦ አካዳሚክ ሜዳይ ሽልማትና ማዕረግ መስጠት፤

፬· ሴሚናሮች ወርክሾፖችና ሲምፖዚየሞችን ማዘጋጀትና ማካሄድ፤

5) "President" means the University President appointed in accordance with Article 10 of these Regulations;

6) "University" means the Jimma University, established in accordance with Article 3 of these Regulations.

3. *Establishment*

1) There is hereby established the Jimma University (hereinafter "the University") as an autonomous higher education institution having its own legal personality.

2) The University shall comprise the following higher education institutions:

(a) Jimma Institute of Health Sciences;

(b) Jimma College of Agriculture;

(c) Other Faculties and Colleges to be established by the Board.

3) The University shall be accountable to the Ministry of Education.

4. *Objectives*

The University shall have the following objectives:

1) to cultivate, expand and transmit knowledge;

2) to provide education that fully develops the personality and strengthens the respect for human dignity, on the basis of mutual respect, trust, mutual understanding and tolerance, and free from ethnic, nationality, gender, religious or other prejudices;

3) to inculcate the dignity of work and dedication for the well-being of the society.

4) to produce competent persons imbued with a sense of social purpose and trained in science and technology, arts and various professions with a view to enhancing the socio economic development of the Ethiopian people;

5) to conduct research and studies in different fields that will help in solving societies' problems and disseminate fruitful results thereof;

6) to provide professional services at regional and national levels with a view to accelerating social and economic developments;

*7) to provide training and consultancey services, by receiving service fee.*

5. *Powers and Duties of the University*

The University shall have the following powers and duties:

1) to establish and run faculties, colleges and other academic and research units;

2) to design and implement undergraduate and postgraduate programmes;

3) to confer academic certificates, diplomas and degrees as well as medals, prizes and titles for excellence and meritorious contributions;

4) to organize and conduct seminars, workshops and symposia;

፭· የአገልግሎት ክፍያ በመቀበልና በገበያ ውስጥ በመግባት የማማከርና ሥልጠና አገልግሎት መስጠት፣
፮· በሀገሪቱ ውስጥና በሌሎች ሀገሮች ከሚገኙ እቻ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋሞችና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ጋር ግንኙነት መመሥረት፣
፯· የትምህርት መጽሔቶችና ጋዜጦች ማቋቋምና ማሠራጨት፣
፰· የንብረት ባለቤት የመሆን፣
፱· ውል የመዋዋል፣
፲· በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፣
፲፩· ዓላማውን የሚያራምዱ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን።

## ክፍል ሁለት

## ስለዩኒቨርሲቲው የፖሊሲና የሥራ አስፈጻሚ አካላት

### ፮· ስለዩኒቨርሲቲው ቦርድ መቋቋም

፩· ዩኒቨርሲቲው በመንግሥት የሚሰየሙ አንድ ሊቀመንበርና ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን አባላት የሚገኙበት ቦርድ ይኖረዋል።
፪· ቦርዱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

### ፯· የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፡

፩· የዩኒቨርሲቲውን የአካዳሚክና የአስተዳደር አጠቃላይ ፖሊሲ ያወጣል ፡ ከመንግሥት ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር በተገናዘበ መልኩ ይወስናል ፡
፪· የዩኒቨርሲቲውን አደረጃጀት ይወስናል ፡
፫· ዩኒቨርሲቲው ወደፊት የሚደራጅበትንና የሚተዳደር በትን ቻርተር እንዲዘጋጅ በማድረግ ለመንግሥት ያቀርባል ፡
፬· የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያፀድቃል ፡
፭· የዩኒቨርሲቲውን ዕቅድና በጀት ለመንግሥት አቅርቦ ያስፀድቃል ፡
፮· የዩኒቨርሲቲውን ም/ፕሬዚዳንቶች ሹመት ለትምህርት ሚኒስቴር አቅርቦ ያስጸድቃል ፡
፯· የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ሁኔታ የሚወስን የውስጥ አስተዳደር ደንብ ከመንግሥት ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር በማገናዘብ ያወጣል ፡
፰· ዩኒቨርሲቲውን በሚመለከት በማንኛውም የዩኒቨርሲቲው አካል ወይም በዩኒቨርሲቲው በተሰጠ ውሳኔ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል ፡
፱· ዩኒቨርሲቲው ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የትምህርት ተቋማት ጋር የሚያደርጋቸውን የአካዳሚክ ስምምነቶች መርምሮ ያፀድቃል ፡
፲· የዩኒቨርሲቲው መለያ ምልክት የሚሆነውን ዓርማ ያጸድቃል፣
፲፩· የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ይወስናል ፡
፲፪· ዩኒቨርሲቲው የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች መንግሥት ባፀደቀው መመሪያ መሠረት ይወስናል ፡
፲፫· የዩኒቨርሲቲውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል ።

5) to provide consultancy and training services, entering the market, charging appropriate fees;
6) to establish relations with local and foreign sister universities, research institutions, and other organizations having similar objectives;
7) to establish and publish academic journals and newsletters;
8) to own property;
9) to enter into contracts;
10) to sue and be sued in its own name;
11) to carry out such other activities as are necessary for the attainment of its objectives.

## *PART TWO*

## *The University Policy and Executive Bodies*

### 6. *Establishment of the University Board*

1) *The university shall have a Board which consists of a chairperson and members to be appointed by the Government.*
2) The Board shall have its own Secretary.

### 7. *Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1) to issue academic and administrative general policies of the University, to render decisions in conformity with Government policies and laws;
2) to determine the organizational structure of the University;
3) to have the Charter of the University which regulates its future organization and administration prepared, and submit it to the Government;
4) to approve rank of a professorship;
5) to have the University plan and budget approved by the Government;
6) to submit for approval the appointment of the vice-presidents to the Ministry of Education;
7) to issue internal administrative regulations which determine conditions of employment and administrations of academic staff of the University with due consideration of Government policies and laws;
8) to review decisions rendered by the University or by any organ of the University;
9) to examine and approve academic agreements made between the University and other local and foreign educational institutions;
10) to approve the emblem of the University;
11) to determine its own rules of procedure;
12) to determine fees to be charged by the University in accordance with directive approved by the Government;
13) to perform such other activities as are conducive to the attainment of the objectives of the University.

፰· የዩኒቨርሲቲው ጉባዔ /ሴኔት/ መቋቋም

፩· ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲው ጉባዔ ይቋቋማል ፡

ሀ) የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ............ ሰብሳቢ

ለ) የዩኒቨርሲቲው ም/ፕሬዚዳንቶች ...... አባላት

ሐ) የየፋኩልቲው ዲኖች ...................... አባላት

መ) የዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር............. አባል

ሠ) በተቋሙ የአካዳሚክ ሠራተኞች የሚመረጡ ሁለት ወኪሎች ............ አባላት

ረ) ሁለት የተማሪዎች ተወካዮች........... አባላት

ሰ) ቦርዱ የሚሰይማቸው አግባብነት ያላቸው ሌሎች የዩኒቨርሲቲው አካላት ......... አባላት

፪· የጉባዔው ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል ።

፱· የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚያወጣው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡

፩· የዩኒቨርሲቲውን የትምህርት ካሌንደር መርምሮ ያጸድቃል ፡

፪· የዩኒቨርሲቲውን ልዩ ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ያጸድቃል፡

፫· ዲግሪዎች ፡ ዲፕሎማዎችና የምስክር ወረቀቶች እንዲሁም ሜዳይና ሽልማቶች የሚሰጡበትን ሁኔታ ይወስናል፡

፬· የተማሪዎች አቀባበልን ፡ የትምህርት ደረጃ አወሳሰንን ፡ የዲሲፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ያወጣል ፡ በነዚህም ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል ፡

፭· አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥና ደረጃዎች አቅጣጫዎችን ይወስናል ፡

፮· የዩኒቨርሲቲውን የአካዳሚክ ሠራተኞች ቅጥር መርምሮ ያጸድቃል ፡

፯· የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለቦርዱ ሃሳብ ያቀርባል ፡

፰· ዩኒቨርሲቲው የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች እንዲወሰን ለቦርዱ ሃሳብ ያቀርባል ፡

፱· የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ይወስናል ፡

፲· በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

፲· የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንቶች ሹመትና ተጠሪነት

፩· የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በመንግሥት ይሾማል ፡ ተጠሪነቱም ለቦርዱ ይሆናል ።

፪· የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንቶች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ይሾማሉ ፡ ተጠሪነታቸውም ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል ።

፲፩· የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የዩኒቨርሲቲው ዋና መሪና አስፈጻሚ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡

፩· የዩኒቨርሲቲውን ሥራ በበላይነት ይመራል፡ ያስተዳድራል፡ ይቆጣጠራል፡

፪· በቦርዱና በጉባዔው የተላለፉ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል ፡

8. *Establishment of the University Senate*

1) There is hereby established the Senate of the University having the following members:

(a) President of the University Chairperson

(b) Vice–Presidents of the University Members

(c) Deans of Faculties............................ Members

(d) Registrar of the University................Member

(e) Two representatives to be elected by the academic staff of the University ................................ Members

(f) Two Students' representatives ......... Members

(g) Other appropriate members to be assigned by the Board ......................Members

2) The Senate shall be accountable to the Board.

9. *Powers and Duties of the Senate*

Subject to directives issued by the Board, the Senate shall have the following powers and duties:

1) to examine and approve the academic calendar of the University;

2) to approve the University's various academic programs;

3) to determine the conditions of conferring degrees, diplomas and certificates, as well as medals and prizes;

4) to set criteria for admission of students, determination of academic standards and graduation, and regulate disciplinary matters; to examine and decide on petitions relating to same;

5) to determine the general directions of conducting of examinations;

6) to examine and approve the employment of academic staff of the University;

7) to recommend to the Board the conferring of the rank of full professorship;

8) to recommend to the Board the amount of fees to be charged by the University;

9) to determine its own rules of procedure;

10) to perform such other activities as may be assigned to it by the Board.

10. *Appointment and Accountability of the University President and Vice–Presidents*

1) The president of the University shall be appointed by the Government, and shall be accountable to the Board.

2) The University vice–presidents shall be appointed according to Article 7 Sub Article (6) of these Regulations; and shall be accountable to the President.

11. *Powers and Duties of the President*

The President shall be the chief executive of the University, and shall have the following powers and duties:

1) to direct, administer and supervise the activities of the University;

2) to follow up the implementation of the decisions made by the Board and the Senate;

፫· የዩኒቨርሲቲውን የአካዳሚክ ሠራተኞች ቦርዱ በሚያወጣው መተዳደሪያ ደንብና መንግሥት ባጸደቀው የደመወዝ ስኬል መሠረት ይቀጥራል ፡ ያስተዳድራል ፡ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲውን የአስተዳደር ሠራተኞች በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ይቀጥራል ፡ ያስተዳድራል ፡

፬· የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ፡ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል ፡

፭· በቦርዱ ሲፈቀድ በዩኒቨርሲቲው ስም የሚደረጉ ማናቸውንም ስምምነቶችና የውል ሰነዶች ይፈርማል ፡

፮· ዩኒቨርሲቲው ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ዩኒቨርሲቲውን ይወክላል ፡

፯· ስለዩኒቨርሲቲው የሥራ እንቅስቃሴ ለቦርዱ በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል ፡

፰· እንደአስፈላጊነቱ ሥልጣኑን በውክልና ይሰጣል ፡

፱· በቦርዱና በጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

፲፪· ስለዩኒቨርሲቲው ም/ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር

፩· የዩኒቨርሲቲው ም/ፕሬዚዳንቶች በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩዋቸዋል ፡

ሀ) የዩኒቨርሲቲውን ሥራ በሚመለከት የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚዳንት ያማክራሉ ፡ ይረዳሉ ፡

ለ) ለእነርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎችን ሥራ ይቆጣጠራሉ፡ በቦርዱና በጉባዔው የተላለፉ ውሣኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላሉ ፡

ሐ) በቦርዱ ፡ በጉባዔውና በፕሬዚዳንቱ ተለይተው የሚሰጧቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ ።

፪· የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በማይኖርበት ጊዜ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ፕሬዚዳንቱን ተክቶ የዩኒቨርሲቲውን ሥራ ይመራል ፡ ያስተባብራል ።

፲፫· የዩኒቨርሲቲው ሌሎች አካላት

የዩኒቨርሲቲው ልዩ ልዩ ፋኩልቲዎች፡ የትምህርትና የምርምር ክፍሎች፡ አመሠራረትና አሠራር እንዲሁም የአመራር አካላት አሰያየም በቦርዱ ይወሰናል ።

ክፍል ሦስት

ልዩ ልዩ

፲፬· በጀት

የዩኒቨርሲቲው በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል ፡

ሀ) ከመንግሥት ከሚመደብለት በጀት ፡

ለ) ዩኒቨርሲቲው ከሚሰበስባቸው የአገልግሎት ክፍያዎች፡ እና

ሐ) ከሌሎች ምንጮች ።

፲፭· የሂሣብ መዛግብት

፩· ዩኒቨርሲቲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል ።

፪· የዩኒቨርሲቲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ ።

3) to employ and administer the academic staff of the University in accordance with the regulations issued by the Board and the salary scale approved by the Government; and employ and administer the administrative staff of the University in accordance with civil service laws;

4) to prepare and submit to the Board the annual plan and budget of the University; and implement same upon approval;

5) to sign any agreement or contract on behalf of the University upon approval by the Board;

6) to represent the University in all its dealings with third parties;

7) to open bank accounts in the name of the University;

8) to submit every three months reports on activities of the University to the Board;

9) to delegate his powers as may be necessary;

10), to perform such other activities as may be assigned to him by the Board and the Senate.

12. *Powers and Duties of the Vice–Presidents*

1) Pursuant to the directives issued by the president, the vice-presidents shall have the following powers and duties:

(a) to consult and assist the president regarding the affairs of the University;

(b) to supervise the activities of the organs accountable to them and follow up the implementation of the decisions and directives issued by the Board and the Senate;

(c) perform such other activities specifically assigned to them by the Board, the Senate, or the President.

2) In the absence of the president, the Academic Vice-President of the University shall direct and coordinate the activities of the University on behalf of the president.

13. *Other Organs of the University*

The establishment and function of the various faculties, academic and research units of the University, as well as the appointment of executive organs shall be determined by the Board.

*PART THREE*

*Miscellaneous*

14. *Budget*

The budget of the University shall be drawn from:

(a) budget allocated by the Government;

(b) fees collected by the University; and

(c) any other sources.

15. *Books of Accounts*

1) The University shall keep complete and accurate books of account.

2) The books of account and financial documents of the University shall be audited annually by the Auditor General or by other auditors designated by him.

፲፮. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ።

፲፯. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

16. *Inapplicable Laws*

Any Regulations or directives inconsistent with the provisions of these Regulations shall not be applicable.

17. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of December, 1999.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE